21 JANUARY 2015 ተጻፈ በ የማ ናግሽ

# በምሥራቁ ዓለም መንገድ ምዕራብ ወያንን ፀጥ ማድረግ!?

በመጪው ግንቦት ወር ለአምስተኛ ጊዜ በሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ ለመወዳደር ፈርጣማ ጡንቻውን አዘጋጅቶ የሚጠብቀው ኢሕአዴግ ገና ተጨማሪ 40 ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ዕቅድ እንዳለው ይናገራል፡፡

በትጥቅ ትግል ደርግን አሸንፎ የሥልጣን ማማ የተቀመጠው ገዥው ፓርቲ፣ ሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ የመቆየት ህልሙ በምርጫ ተፎካክሮ የሚያሸንፈው <<ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ በቅርብ ጊዜ አይፈጠርም>> ከሚል ትንተና የተነሳ መሆኑን፣ በአራተኛ ዙር ምርጫ ማግስት በወጣው የፓርቲው የርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ማብራሪያ በሆነው አዲስ ራዕይ መጽሔቱ አትቶ ነበር፡፡ በእርግጥ አገላለጹ አወዛጋቢ ቢሆንም በ<<አውራ ፓርቲ>>ነት ለመቀጠል ዕቅድ አለው፡፡

ኢሕአዴግን ለዓመታት በሊቀመንበርነት የመሩት ሟቹ አቶ መለስ ዜናዊ ይዘውት ብቅ ያሉት <<የመተካካት ፖሊሲ>> አሮጌውን አመራር በአዲስ አመራር በመለወጥ ለማደስ በማሰብም ጭምር ነው፡፡ ዓላማውም ድርጅቱን ከመበስበስ አደጋ ለመከላከልና ሥልጣን ላይ ዘለግ ላለ ጊዜ ለመቆየት ነው፡፡

ኢሕአዴግን ከመነሻ ጀምሮ በጥርጣሬ የሚመለከቱ ተቃዋሚ ወገኖችና የምዕራባውያን የፖለቲካ ተንታኞችን ግን እሳቤውን በተቃራኒ ይመለከቱታል፡፡ ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ የመቆየት አባዜ እንዳለበት፣ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም ተቀናቃኞችንና የፖለቲካ ተሟጋቾችን ፀጥ በማድረግ የይምሰል ምርጫ በማካሄድ እንደሚያምን ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ የአስተሳሰብ ርቀቶችና አድማሶች በፖለቲካ ትንተና ዓይን ሲታዩ፣ ኢሕአዴግ የሚከተለው የ<<ልማታዊ መንግሥት>> ሞዴል ልማትን በአጭር ጊዜ ካሳኩ አገሮች ልምድና ተሞክሮ በመጥቀስ ተቀባይነቱን ለመጨመር ማለሙ ይነገራል፡፡ ይኼም የርዕዮተ ዓለምና የልማት አቅጣጫ የዘመናችን ኃያላን መንግሥታት ከሆኑት ያለውን ወዳጅነት ርቀትና ቅርበት የሚወሰንበት በመሆኑ፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውም ከዚሁ አስተሳሰብ የተቀዳ ነው፡፡

ከሩሲያ ወደ እስያ

በአፄው ዘመን ከምዕራባውያን በተለይ ደግሞ ከአሜሪካ ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበራት ኢትዮጵያ፣ ከአብዮቱ በኋላ ሥልጣን ላይ የወጣው ደርግ ተቀናቃኞቹን በጦርነት ሜዳ ለማሸነፍ ወዳጅ ያደረገው የቀድሞዋን ሶቪየት ኅብረት ነበር፡፡

ወቅቱ በምዕራቡ ዓለምና በታላቋ ሶቪየት ኅብረት በሚመራው የሶሻሊስት ቡድን መካከል የቀዝቃዛ የዓለም ጦርነት ይካሄድበት ነበር፡፡ ዋነኞቹ ተቀናቃኞች በነበሩት በሕወሓት (በኋላም በኢሕአዴግ) እና በደርግ መካከል የርዕዮተ ዓለም ልዩነት እምብዛም አልነበረም፡፡ በእርግጥ ሕወሓት ሲከተለው የኖረው የግራ ዘመም አስተሳሰብ ምርጥ የተባለውንና ገበሬውን መሠረት ያደረገ፣ ኑሮውንም ለመለወጥ መሠረት እንደጣለ የሚታመንበት የአልባንያውን ዓይነት ነበር፡፡ ከቻይናም ጋር እምብዛም የሚራራቅ አልነበረም፡፡

በ 1980 ዎቹ መጀመሪያ በምዕራቡ ዓለም አሸናፊነት የቀዝቃዛው ጦርነት ሲጠናቀቅ፣ ኢሕአዴግም የፖለቲካ አቋም ሽግሽግ ለማድረግ ተገዶ ነበር፡፡ በመሆኑም በሁለት ጫፎች ላይ የሚገኙትን አስተሳሰቦች (የግራና የቀኝ ዘመም) አጣጥሞ ይሄዳል ተብሎ የታመነበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ነበር ዘግየት ብሎ በኢሕአዴግ ተግባራዊ የተደረገው፡፡

ከመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታት ጀምሮ በምዕራባውያን አገሮችና በመሰሎቻቸው በተቋቋሙት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ነፃ ገበያን ተግባራዊ እንዲያደርግ፣ ወታደሩን እንዲበትንና የመንግሥት ወሳኝ የልማት ተቋማት ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት እንዲሆኑ ጭምር የሚያስገድደው <<የመዋቅራዊ ለውጥ ፕሮግራም>> በመርህ ደረጃ ቢቀበለውም፣ ይዞት ከቆየው አስተሳሰብ ተቃራኒ ሆኖ ተግባራዊ ማድረግ አቅቶት በዕርዳታና በፖሊሲ ሪፎርም ማድረግ መንታ መንገድ ላይ እንደነበር ብዙ ታዛቢዎች ጽፈዋል፡፡

በአብዛኛው የኢሕአዴግን ፖሊሲ በማመንጨት ይታወቁ የነበሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም፣ ከባዶ ካዝና ጋር ያገኙትን ቤተ መንግሥት ይዘው ፖሊሲያቸውን አልቀበልም ማለት የከበዳቸው ይመስል፣ የምዕራባውያን ዕርዳታና ብድርን ሙሉ በሙሉ ሳያጡ የፖለቲካ ጫናውን የሚቋቋሙበት መፍትሔ ለማፈላለግ ሦስተኛ አማራጭ ዓለም ፍለጋ ውስጥ ገቡ፡፡

ምዕራቡን በምሥራቁ

ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት በማሸነፍ ዴሞክራሲን፣ መድበለ ፓርቲን፣ እንዲሁም ነፃ ገበያን መሠረት ያደረጉ አስተሳሰብ አራማጆቹ አሜሪካና በአጠቃላይ የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያ የፖለቲካ አቅጣጫ ወደሚፈለገው እየነፈሰ ማየት አልተቻላቸውም፡፡ ገና ከጅምሩ ምርጫ ማካሄድ፣ ሐሳብን በነፃነት መግለጽ፣ በነፃነት መደራጀትና መቃወም

የመሳሰሉ ጉዳዮችን በቅድመ ሁኔታን በማስቀመጥ፣ የሚሰጡትም ድጋፍ በእነዚህ መሥፈርቶች ይለካ ነበር፡፡ የኒዮ ሊብራሊዝምን አስተሳሰብ በእጅጉ የሚጠሉትና በይፋ በኢትዮጵያ ፓርላማ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃም እንዲጠላ በማድረግ ሌላ አማራጭ መንገድ ሲፈልጉ የነበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ እስያ በተለይ ደግሞ ወደ ቻይና፣ ታይዋን፣ ደቡብ ኮሪያና በኋላም ወደ ህንድ ያቀኑት ገና በጠዋቱ ነበር፡፡ ቱርክም እንዲሁ ተካትታለች፡፡

ባለፉት 20 ዓመታት በደሃና በሀብታም መካከል የነበረው ልዩነት እየሰፋና ጥቂት ሀብታሞች ብቻ በዓለም የሀብት ማማ ላይ እንዲሰፍሩ ያደረገውንና የመንግሥት የኢኮኖሚ ሚና እጅግ ዝቅተኛ እንዲሆን የሚጠይቀውን የነፃ ገበያ አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ የሚጻረርም ባይሆን፣ አማራጭ አስተሳሰብ በዚሁ በምሥራቅ እስያ እየበቀለ ነበር፡፡ ይህ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ልማት ከዲሞክራሲ ቀድሞ እንዲመጣ የሚያዘው የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ፣ ኢሕአዴግ ቀድሞ ከሚከተለው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚጣጣም ሆኖ ስለተገኘ መመርያው አደረገው፡፡ የመንግሥትም ሚና ከፍ ያለ ሆነ፡፡

የኢሕአዴግ የልማት አቅጣጫ ዴሞክራሲን ወደ ጐን ያደረገ ነው በሚል በተለያዩ ምሁራን የሚተች ሲሆን፣ ይህንን ደግፈው የሚጽፉም አልጠፉም፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ የኖርዌይ ተቋም የሆነው ኢንተርናሽናል ሎው ኤንድ ፖሊሲ ኢንስቲትዩት፣ ከኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ባሳተመው “Ethiopia’s International Relations: The Foreign Policy Making and Determinant of an Emerging Giant” በሚለው መጽሐፍ ከተካተቱት መካከል፣ በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ፋንቱ ቸሩ ያቀረቡት ጥናት ይገኝበታል፡፡

ይህ “Ethiopia’s Foreign Policy Towards ‘Old’ and ‘New’ Development Partners” የሚለው ጥናታዊ ጽሑፍ፣ የኢሕአዴግ ፖሊሲ ገና በትጥቅ ትግሉ ወቅት ጀምሮ የነበረውን አስተሳሰብ የሚዳስስ ሲሆን፣ የኢሕአዴግ መንግሥት በዚሁ የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ የምዕራባውያን ተፅዕኖ እንዴት እንደተቋቋመ የሚያሳይ ነው፡፡ ያልታተመውና ብዙ ሲያነጋግር የነበረው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፍን ጭምር የሚተነትነው የፕሮፌሰር ፋንቱ ጽሑፍ፣ በቅርቡ በደሳለኝ ሆቴል መጽሐፉን መሠረት በማድረግ በተደረገው የውይይት መድረክ ላይም ቀርቦ ነበር፡፡

በ 1980 ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ተጀመረ ያሉት የምዕራባውያንን ፖሊሲ የሚከላከል አስተሳሰብ ነበር ይላሉ፡፡ እሱም የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትን ወደ ኢኮኖሚያዊ እንዲያዘነብል በማድረግ፣ በማደግ ላይ የነበሩትን የምሥራቅ እስያ አገሮች በመቀመር የተወሰነ የእፎይታ ጊዜ ማግኘት ላይ ያተኮረ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

<<የዕርዳታ››ን አባዜ አስቀርቶ ወደ አጋርነት ያዘነብላል ያሉት የኢትዮጵያና የምሥራቅ እስያ አገሮች ግንኙነት የተጀመረው፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቻይና በማምራታቸው የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡

በእርግጥ ከአሥር ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ. በ 1994 አካባቢ የተቀረፀው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ ኢትዮጵያ ከቀደሙት (Traditional) የኢትዮጵያ ወዳጆች (ምዕራባውያን) እና ከአዲሶቹ ጋር ያላት የውጭ ስትራቴጂ ተብራርቷል፡፡

ፕሮፌሰሩ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በመመረቂያ ጽሑፋቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰነድን ከኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ አንፃር እንደተነተኑት አስታውሰው፣ አገሪቱን በተቻለ መጠን ከምዕራባውያን ጫና ነፃ ያደረገ የውጭ ጉዳይ አቅጣጫ ‹‹በልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ›› የቀረፀ ነበር በማለት ይሟገታሉ፡፡ ይኼም በየደረጃው የአገሪቱ ኢኮኖሚ ለዘመናት ገብቶበት ከቆየው አዘቅት ወጥቶ ወደ ተሻለ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር መርዳቱን ተከራክረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከቻይና፣ ከህንድና ከቱርክ ጋር ያላት የኢኮኖሚ ግንኙነትና አጋርነትም ከዜሮ ተነስቶ አሁን ወዳለበት ደረጃ እንዴት እንደ ደረሰ ያመለክታሉ፡፡ ለዚህም በተለይ ከቻይና ጋር የፓርቲ ለፓርቲ ቅርብ ግንኙነቱ ምን ያህል እንደረዳቸው ተንትነዋል፡፡ ‹‹የቻይናውያን በኢትዮጵያ በብዛት መገኘት የኢትዮጵያ መንግሥት ምዕራባውያንን በራስ መተማመን መንፈስ እንዲቀርብ ረድቶታል፤›› ይላሉ፡፡

<<ለምዕራባውያን አባታዊ ትዕዛዝ በቀላሉ ተጓዥ ያልሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ፖሊሲ አውጪዎችም፣ ዛሬም የልማታዊ መንግሥት ሙዚቃ ብቻ የሚያዳምጥ ጆሮ ነው ያላቸው፤›› እንደ ፕሮፌሰሩ እምነት፡፡

በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ተፅዕኖ ሥር ነበር ያሉት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አቅጣጫ በፓርቲና በመንግሥት ምንም ልዩነት አልነበረውም ይላሉ፡፡

በሚሰጡት ዕርዳታ መጠን የፖለቲካ ተፅዕኖ ማሳደር ያልተሳካላቸው አሜሪካና አውሮፓ ኅብረት (አባላት አገሮችም) ኢትዮጵያ የምትከተለው መንገድ አልያዝ አልጨበጥ ቢሆንባቸውም፣ ‹‹የሥርዓቱ ወለል ዴሞክራሲ ላይ ቆመ፡፡ ይልቁንም ያለኢትዮጵያ በአካባቢው መንቀሳቀስ አልተቻላቸውም፤›› ይላሉ፡፡ የአገሪቱ መዋቅርና ቢሮክራሲ በጠንካራ መሠረትና ዘላቂ ራዕይ ላይ የተመሠረተ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

የዕርዳታ ፖሊሲያቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ያስመዘገበውን ዕድገት ማስገንዘብ ይችል እንደነበር ማረጋገጥ ያቃታቸው ምዕራባውያንም፣ በአንድ ድምፅ የሚናገሩት አቋም እንደሌላቸውም ጠቁመዋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ለውጥ ከገመቱት ውጪ እንደሆነም ይከራከራሉ፡፡

በመጠኑ ላይ ልዩነት ቢኖራቸውም፣ በኢትዮጵያ ባለፉት አሥር ዓመታት በሁለት አኃዝ የተመዘገበውን ዕድገት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ይመሰክራሉ ይላሉ፡፡

በመሆኑም ‹‹የውጭ ፖሊሲ ለኢሕአዴግ እንዲያው በውጭ ግንኙነት ብቻ አይደለም፡፡ ጥብቅ ፖለቲካ ነው፤›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ድርጅቱ የሚመራት አገር ሉዓላዊነቷ እንደተጠበቀ፣ ግንኙነቱም ሳይቋረጥ ለዓለም አቀፍ መርሆች ተገዥ ሆኖ፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ማመንጨትም ላይ የተመሠረተ ነው፤›› የሚል ድምዳሜም ሰጥተዋል፡፡

በዲሞክራሲያዊ ምርጫ፣ ነፃ ፕሬስና በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ትችት የሚያቀርቡ አብዛኞቹ ምዕራባውያን አገሮች በተግባር ግንኙነታቸውን ከማጠናከር ውጪ አሉታዊ የሆነ ዕርምጃ ሲወስዱ አይታዩም፡፡ ተቃዋሚዎችም በዚህ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ በተደጋጋሚ ይደመጣሉ፡፡